በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ግንቦት 17 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 69ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 69ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የተዘጋጀ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ በሃገሪቱ የካሳ አዋጅ ተደንግጎ በስራ ላይ ከዋለ 13 ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑ ወቅታዊነት የጎደለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በከተማም ሆነ በገጠር ባለይዞታዎች ለህዝብ ጥቅም መሬት እንዲለቁ ሲደረግ የተነሺዎችን በህገ መንግስቱ የተቀመጡ የመብት ድንጋጌዎች ባከበረ እና በመሬት ዘርፍ መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ርብርብ ለመደገፍና የመንግስትን ልማታዊነት ለማረጋገጥ በሚያስችል አግባብ እንዲሆን አዋጁን አሻሽሎ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ማስተካከያዎችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የጉሙሩክ አዋጅን ለማሻሻል ተዘጋጅቶ በቀረበ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን ነባሩ አዋጅ ዲክላራሲዮን እንዲሻሻልና እንዲሰረዝ የማይፈቅድ በመሆኑና እንዲሁም የንግድ ስራን ከማሳለጥ/ease of doing business/ አንጻር በርካታ ችግሮች የነበሩበት መሆኑን በመግለጽ የገቢዎች ሚኒስቴር የማሻሻያ አዋጁን አዘጋጅቶ እንዳቀረበ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ የማሻሻያ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡
3. በመጨረሻም ምክር ቤቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዘጋጅተው በቀረቡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና በእስራኤል መንግስት መካከል በጉሙሩክ ጉዳዮች፣ በቱሪዝም ዘርፍ እና በግብርና ዘርፍ ለመተባበር የተፈረሙ ስምምነቶችን ለማጽደቅ በቀረቡ ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቷል፡፡ ስምምነቶቹ ቀልጣፋ የጉሙሩክ አስተዳደርና ውጤታማ የጉሙሩክ ህጎች አተገባበር እንዲኖር፣ በቱሪዝም መስክ የተሰማሩ ባለሙያዎች ልምድ እንዲለዋወጡ በማስቻልና የቱሪዝም መዳረሻቸውን ለማስተዋወቅ እንዲሁም አገራችን በግብርናው ዘርፍ በተለይም በዘመናዊ አመራረት፣ በውሃ አጠር መስኖ ስራዎች እና በባዮቴክኖሎጂ ዘርፍ ከእስራኤል ጋር የምትሰራውን ስራ ህጋዊ መሰረት ለማስያዝ የሚያግዙ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ምክር ቤቱም ስምምነቶቹን ለማጽደቅ በቀረቡት ሶስት ረቂቅ አዋጆች ላይ ተወያይቶ ይጸድቁ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

//